# ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ለኢትዮጵያዊያን ህጻናትና ታዳጊዎች መልዕክት

የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን ሕጻናትና አዳጊዎች ዛሬ የኮሮና ወረርሽኝን ለመከላከል መንግሥታችሁ ምን እየሠራ እንደሆነ፣ ከእናንተም ምን እንደሚጠበቅ ለእናንተ ለመግለጥ እፈልጋለው:: ይህ መንግሥት የእናንተ የልጆችም መንግሥት ነውና:: ልጆች የኮሮና ቫይረስ በዓለም ላይ የመጣ ወረርሽኝ ነው:: ከቻይና ተነሥቶ ዓለምን እያዳረሰ ነው:: ብዙ ሀገሮች ዜጎቻቸውን በሞት አጥተዋል:: በኛም ሀገር 126 ያህል ኢትጵያውያን በቫይረሱ ተይዘውብናል:: አካላዊ ርቀትን መጠበቅ አንዱ መከላከያ ነው:: አካላዊ ርቀትን መጠበቅ ማለት ከሌላ ሰው በአራት የልጆች ርምጃ ርቆ መቆምና መቀመጥ ነው:: እጅን ደጋግሞ በሳሙና መታጠብ ሁለተኛው መከላከያ ነው:: ልጆች ጠዋት ስትነሡ፣ ስትጫወቱ ፣ ከተጫወታችሁ በኂላ፣ ከምግብ በፊትና በኂላ፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በሳሙና ታጠቡ:: ስትታጠቡ ጣታችሁን፣ መዳፋችሁን፣ በጣታችሁ መካከል ፣ የእጃችሁን መዳፍ ፊትጋችሁ በውኃና በሳሙና ታጠቡ:: ትምህርት ቤት ተዘግቶ ቤት ነው ያላችሁት:: አደራ ከቤት አትውጡ:: ትቤት የተዘጋው በንክኪ ምክንያት እንዳይተላለፍባችሁ ብለን ነው:: እናንተ ለነገዋ ኢትዮጵያ በጣም ታስፈልጓታላችሁ:: ስለዚህ ጤናችሁን ጠብቁ:: ቤት መዋል ሊሰለቻችሁ ይችላል:: ግን እንዳትታመሙብን፣ እንዳትሞቱብን ብለን ነው:: ቤት ስትሆኑ አጥኑ፣ መጽሐፍ አንብቡ፣ አካላዊ እንቅስቃሴ ሥሩ፣ የልጆችን ጨዋታ ተጫወቱ:: ተጠንቀቁ እንጂ አትጨነቁ:: ዐዋቂዎች የተለያዩ መረጃዎችን ሲነጋገሩ እየሰማችሁ ልትጨነቁ ትችላላችሁ:: ወላጆቻችሁ ሲወያዩ እናንተን እንዲያስቡ እንነግራቸዋለን:: ነገሩን በእናንተ ቋንቋ እንዲያስረዷችሁ አደራ እላቸዋለሁ:: አይዟችሁ፤ ይሄን ከባድ ጊዜ እናልፈዋለን፤ ፈጣሪ እናንተን ይሰማልና ለኢትዮጵያ ጸልዩ::